# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ፕሮግራም

## SSL ምንድነው?

- የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ማለት ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መካከል ለሚገኙ ተማሪዎች የስቴት የመመረቂያ መስፈርት/መመዘኛ ነው።
- ተማሪዎች ለማህበረሰቡ በበጎፈቃደኝነት በሚያበረክቱት ትርጉም ያለው አገልግሎት ትምህርት ያገኛሉ።
- የአገልግሎት ትምህርት ስለ ዜጎች/የዜግነት እዉቀት፣ ስለዜጎች ተሳትፎ፣ ስለአካዴሚያዊ ስኬት፣ እና የተማሪዎች ባህርያዊ እና ማህበራዊ እድገትን ያዳብራል/ያበረታታል።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሚያዝናና ሁኔታ የተቀረጸ እነዚህን ሁሉ መረጃዎች ለማካፈል የSSL ፕሮጀክቶች ናሙናዎችን የሚያካትት አጭር ቪድኦ አለው። ይመልከቱት! http://bit.ly/mcpssslvideo

## የሜሪላንድ (MD) ስቴት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመዘኛዎች-መስፈርቶች

- የሜሪላንድ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሙሉ ሰባአምስት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት "75 SSL hours" ሠአት ያገኛሉ።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች **5ኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ ካለው ሠመር ጀምሮ በዚህ የመመረቂያ መስፈርት ላይ ይሠራሉ።** ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከሚጨርሱ ድረስ እየሰሩ ሠዓት ማግኘት ይችላሉ።
- ከ6ኛ ክፍል በኋላ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚገቡ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው ሠዓት መጠን የተሸጋሸገ ይሆናል።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት እንዴት ለማግኘት ይችላሉ?

ተማሪዎች ለምረቃ የሚያስፈልገዉን "75 SSL hours" ለማግኘት የሚችሉት በሁለት መንገድ ነው፡-

1. **ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ኮርሶች በስኬታማነት ሲያጠናቅቁ "45 SSL hours" ለማግኘት ይችላሉ። በክፍል ዳሰሳ/ምርምር እና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች መምህራን ሊመሯቸው ይችላሉ።**

| | |
|---|---|
| 10 ሠዓት | የ6ኛ ክፍል ሳይንስ |
| 10 ሠዓት | የ7ኛ ክፍል እንግሊዝኛ |
| 10 ሠዓት | የ8ኛ ክፍል ማህበራዊ ጥናት |
| + 15 ሠዓት | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር |
| **45 ሠዓት በአጠቃላይ በትምህርት ቤት ክፍሎች - ትምህርቶች ዉስጥ** | |

2. **30 የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ከትምህርት ቤት ውጪ (ለትርፍ ያልተቋቋመ ኤጀንሲ)**

   ተማሪዎች Montgomery County Volunteer Center (MCVC) ድረ-ገጽ በመጎብኘት የ MCPS SSL ድርጅቶችን እና እድል ለማግኘት ይችላሉ (www.montgomeryserves.org) ተቀባይነት ያላቸው የ SSL እድሎች። (ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሁሉም የመመረቂያ ቆብ እና “MCPS SSL” ምልክት ይኖራቸዋል። እባክዎ አባሪ በተደረገው ጽሑፍ ላይ የ MCVC ድረ-ገጽ በመፈለግ ፍንጮችን ያግኙ።)

   ተማሪዎች የራሳቸውን ለትርፍ ያልተቋቋሙ ኤጀንሲዎችን ለማግኘት ይችላሉ (የአካባቢ፣ የስቴት፣ ወይም አገር አቀፍ) MCVC ድረ-ገጽ ላይ የሌለ እና ይህንን ቅጽ በመሙላት **MCPS Form 560-50፦ የተማሪ የግል የአገልግሎት ትምህርት መጠየቂያ ቅጽ (http://bit.ly/SSLPreApproval)፣** ለትምህርት ቤታቸው የተማሪ አገልግሎት ትምህርት አስተባባሪ (SSL coordinator) (በትምህርት ዓመቱ ውስጥ) ወይም ለ ssl@mcpsmd.org (በሠመር ወቅት) አገልግሎት ከመጀመሩ አስቀድሞ እንዲፀድቅ ማቅረብ።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት "MCPS SSL" እድሎች በሙሉ መሆን ያለበት፡-

- ለትርፋማነት ያልተቋቋመ የተመዘገበ ኤጀንሲ
- የኃይማኖት ተቋም ያልሆነ/ከሃይማኖት ጋር ግንኙነት የሌለው ምድራዊ/ዓለማዊ
- በህዝብ መገልገያ ቦታ
- ክትትል/ቁጥጥር ተደርጓል (በወላጅ ወይም በዘመድ አይደለም)
- ለበጎፈቃድ አገልግሎት ብቻ (አይከፈልም)
- በቀን ከ8 ሠዓት ያልበለጠ

**የMCPS ቅጽ 560-51: የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ** http://bit.ly/SSLReflection

ይህ ቅጽ የሚያገለግለው የተማሪን የአገልግሎት ትምህርት ሠዓት ለመመዝገብ እና ለትምህርት ቤት የተማሪን የአገልግሎት ትምህርት አስተባባሪ እንዲገመግም/እንድትገመግም እና በተማሪ SSL ሠዓት ላይ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ የሚሰጥ ነው።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ የ SSL ሠዓት ለማግኘት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ለመወሰን ይህንን የቅደም ተከተል ፍሰት/ስዕላዊ መግለጫ ተጠቀም(ሚ)።




**ልዩ የሆነ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መስፈርት ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ሁለት አይነት የ SSL ሽልማቶች አሉ።**

| ክፍል | ሽልማት |
|---|---|
| 6ኛ፣ 7ኛ፣ እና 8ኛ ክፍሎች | **ስለ አገልግሎት ትምህርት ከሱፐርኢንተንደንት የሚሰጥ ሽልማት**<br>(በሚድል ስኩል/መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለ(ች) የተገኘ 75 ሠዓት፣ አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጠ) |
| 12ኛ ክፍል | **ሽልማት የሚገባው አገልግሎት ሠርተፊኬት/በችሎታ የሚሰጥ አገልግሎት ሠርተፊኬት**<br>(በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመመረቂያ/ሲንየር ዓመት የተገኘ 260 ሠዓት) |

**የ SSL አገልግሎት ቅጾች በሙሉ** በወቅቱ የትምህርት ዓመት እና ከአሁኑ የትምህርት ዓመት ቀደም ባለው በሠመር ለተሰጡ አገልግሎቶች **ያስፈልጋሉ** ተሞልተው ለትምህርት ቤት የተማሪ ሥራ አገልግሎት ትምህርት አስተባባሪ **ጁን ከመጀመሪያው ዓርብ ቀን በፊት** መቅረብ አለባቸው።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃድ ማእከል ድረ-ገጽ፡** www.montgomeryserves.org

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ድረ-ገጽ፡-** www.mcps-ssl.org

**ይፈልጉን!**

**@mcpsvolunteers**